የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፹፪
አዲስ አበባ ጥቅምት ፲ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.82
ADDIS ABABA 20th October, 2020

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳፭/፪ሺ፲፫ ዓ.ም

ለኮሮና ቫይረስ (COVID-፲፱) አስቸኳይ ጊዜ ምላሽ የበጀት ድጋፍ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ............................................ገጽ ፲፪ሺ፰፻፸፫

**Content**

Proclamation No.1225/2020

Export-Import Bank of Korea Loan Agreement for financing COVID-19 Emergency Crisis Response Budget Support Program Ratification Proclamation ..........................................................Page 12,873

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳፭/፪ሺ፲፫

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለኮሮና ቫይረስ (COVID-፲፱) አስቸኳይ ጊዜ ምላሽ የበጀት ድጋፍ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፵ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (አርባ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል ሰኔ ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መስከረም ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም ባካሄደው ፬ኛ አስቸኳይ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO. 1225/2020

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE EXPORT-IMPORT BANK OF KOREA

WHEREAS, the Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export-Import Bank of Korea stipulating that the Export-Import Bank of Korea provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of Forty Million United States Dollar (USD 40,000,000) for financing COVID-19 Emergency Crisis Response Budget Support Program, was signed in Addis Ababa on 30th day of June, 2020;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its 4th urgent session held on the 22nd day of September, 2020

NOW, THERFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለኮሮና ቫይረስ (COVID-፲፱) አስቸኳይ ጊዜ ምላሽ የበጀት ድጋፍ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳፭/፪ሺ፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡"

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል ሰኔ ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር ETH-9 በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፵ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (አርባ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት ፲ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Export-Import Bank of Korea Loan Agreement for financing COVID-19 Emergency Crisis Response Budget Support Program Ratification Proclamation No. 1225/2020".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Number ETH-9 signed in Addis Ababa on 30th day of June, 2020 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export-Import Bank of Korea is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of Forty Million United States Dollar (USD 40,000,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the *Federal Negarit Gazettee.*

**Done at Addis Ababa, on this 20th day of October, 2020**

**SAHILEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**